# ዋልድባ

ከነቅዐ ጥበብ

ታላቁ የጽድቅ አምባ፣
በአታቸው የቅዱሳን፣ የመናኞቹ የነ አባ፣
“ዘእንበለ ፈላሲ፣ እይግባዕ ነጋሢ፣
“ዘእንበለ ፈላሲ፣ እይግባዕ ሐራሲ፣"*
በሚል የቃል ኪዳን ሕግ፣
ለዘመናት የኖርህ፣ ባለማዕረግ፣
“ዳርህ እሳት፣ መሀልህ ገነት፣"
ተብሎ ተከልሎ፣
እንዳልኖረ፣ እራሱን ችሎ፣
እንደ ዮዲት ጊዜ፣ እንደ ግራኝ፣
ታሪክህን የሚያጠፋ፣ ጨካኝ፣
ደፋር፣ ከሃዲ፣ ወያኔ፣
እምነት የሌለው፣ አረመኔ፣
ክብርህ. ታሪክህን ለመግሠስ፣
ያባቶችህን አፅም፣ ሊያፈልስ፣
ታጥቆ መነሳቱን ሰምተናል፣
ያንተንም አቋም፣ አውቀናል፣
የነአባይ ፀሐይዬ፣ አፍራሽ ተልዕኮ፣
ቀደም ብሎም ገብቶናል፣
የቤተክህነትም ምልምሎች፣
ያይጥ ምስክር ድንቢጦች፣
የእብድ ዱላ አቀባዮች፣
አነጋገራቸው ገርሞናል፣
በክህደታቸውም አዝነናል፣
አይዟችሁ አባቶቻችን! የሳሙኤል አምላክ ያውቅልናል!

አዎ! ሳሙኤል ዘዋልድባ፣
ኃያሉ መነኮስ፣ ታላቁ አባ፣
በአጸደ ነፍስም፣ ይጋደላል፣
በፀሎት በርቱ፣ ብሎናል፣
እኛም አብረን፣ <u>ታንት</u> ብለናል፣
አሁንማ ምን ቀርቶናል፣
በነፍሳችንም ያዝብናል?!

---

- ትርጉም፡ ያለመናኝ ንጉሥም ሆነ ገበሬ እንዳይገባበት።